# ዶ/ር ካትሪን ሃምሊን የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታ በ96 ዓመታቸው አረፉ

March 19, 2020

ሰው መኾን አይሞትም



ዓለማችን የብዙ ዓይነት ሰዎች የትወና መድረክ ናት። ርጎሩጎ እና ጨካኝ፣ ታጋሽ እና ብስጩ፣ ጀግና እና ፈሪ፣ ሳምራዊ እና ሌዋዊ፣ የዋኅ እና መሰሪ፣ ደሀ እና ሀብታም፣ ምሁር እና ማይም፣ መሃይም እና አረሜ፣ እውነተኛ እና መልቲ . . .።

ይሁን እንጅ ሁሉም የማይቀሩበት የማያረፍዱበት አንድ ተመሳሳይ ቀጠሮ አላቸው። ዐረፍተ ዘመን ይጎታቸዋል። ግን ከሞታቸው በኋላ ውጤታቸው ለየቅል ነው። አንዱ በግብረ ሠናዩ የተነሣ ከየሰው አፍ የማይለይ ጣፋጭ ሲኾን ሌላኛው ጎምዛዛ ለመጥራት የሚያንገሸግሽ ይኾናል።




ዶ/ር ካትሪን ከጣፋጮች ባለስሞች አንዷ ናቸው። በሀገራችን ኢትዮጵያ ስቃይ ለጸናባቸው ለምስኪኖች

እኅቶቻችን እንደገና መወለድ ምክንያት የኾኑ የደግ ደግ እመቤት ናቸው። በእምቦቃቅላ ዘመናቸው “ለትዳር የተሸጡ” ሴቶች ከሚደርስባቸው ክፉ ስቃይ ያርፉ ዘንድ ፈጣሪ የላካቸው የሰው ደርዝ ናቸው።




በትውልድ በነገድ እንዲያው በአጠቃላይ በሥጋ አቆጣጠር ሩቃችን ናቸው። ሰው በመኾን ግን ከቅርባችን። ሰውነት ድንበር የለበትም። ፈረንጅ ኾነው የኢትዮጵያውያን ሕፃናት አንእስት ሕማም ያመማቸው የሰው ከፍታ ናቸው። እኒህ ክብርት እመቤት ፺፮ ዓመታት የኖሩባትን ምድር ተሰናብተዋታል። ከላይ ደጅ ፈጣሪ በልዩ ምሕረቱ እንዲቀበላቸው ጸሎቴ ነው። አውሮጳዊ ኾኖ ተወልዶ ለኢትዮጵያ መኖር እና መሞት

በመባረክ የተገኘ ጸጋ እንጅ ሌላ ምን ይኾናል? ጀምስ ብሩስን እና ፍራንሲስኮ አልቫሬዝን ባየንበት እነ ሲልቪያ ፓንክረስትን እና ካትሪን ሀምሊንን ማየታችን ይደንቃል። አልፎንዞ ሜንዴዝን እና ፓኤዝን ባየንበት እመቤት ካትሪን ማየት ደስ ይላል።

ዶ/ር ካትሪን ሀምሊን በብዙዎች የልብ ዙፋን ላይ ነግሠው ይኖራሉ። የሠሩት የሰውን ሥራ ነውና። የበጎ ሰው ሽልማት ድርጅት በጎ ሰው ናቸው ብሎ ሸልሟቸዋል። ሐውልትም ቆሞላቸዋል። በጎነት ስፍራው ከመቃብር በላይ ነው። በላይ በሰማይ በታች በምድር ይከብራል።

ሰው መኾን አይሞትም።

ዓባይነህ ካሤ